# ከዋናው መስሪያ ቤት የመጡት እንግዳ
# ክፍል ሁለት
# ካለፈው የቀጠለ

ከበልጅግ አሊ

የሊቁ የቅርብ ጓደኞች ናሰርና ገረመው ቢሆኑም የሊቁ ጥሩ ጠባይ ከማንም ጋር የሚያኖረው ስለነበር እንደ እነርሱ አይቅረቡት እንጂ ሌሎችም ጓደኞች ነበሩት። ናስርና ገረመው ሁለቱም ምንም የሊቁ ጓደኞች ቢሆኑም ምንም የሚያመሳስላቸው የጋራ ጠባይ ስላልነበራቸው እንዲያውም የሚተዋወቁ አይመስሉም ነበር።አንዳንዴ ብቻ ሻይ ተክሉ ውስጥ ሲገናኙ ናስር ገረመውን ቀፎው እንዴት ነው ይለዋል ማለት ጠጁ የሚሰራበት ማር ለማለት ነው። ገረመው ደግሞ ማሳው ውሃ አገኘ እንዴ ይለዋል የናስር ጫትን ለማሽሟጠጥ በዛው ተሳስቀው ይለያያሉ።

ናስር የጉመሮ ሻይ ተክል ቋሚ ሰራተኛና  የትራክተር ሾፌር ሲሆን ወደ ጉመሮ የመጣው ከከፋ ክፍለ ሃገር ነው። የአጋሮ ልጅ ጫት ጥርሱን ያበለዘው ሲሆን በሚቀጥለው የሚያጨስውን ሲጋራ ከጆሮው ግንዱ ላይ ሰክቶ መዞርን የሚወድ፣ አማርኛ ሲነጋገር ከኦሮሞኛ ጋር ስለሚደባልቅ ቢናገር የማይጠገብ ነው።ትራክተር ሲነዳ ጠዋት ጠዋት ሰው ማነጋገር አይወድም።ከሰአት በኋላ ግን ከየት እንደሚያገኘው የማይታወቅ ጫቱን ከጎረሰ  ጠዋት እንዲዚያ ሰው ማነጋገር የማይወደው ሰው ከሰአት በኋላ አላፊ አግዳሚውን እያሳቀ ሰላም ማለትን ያዘወትራል።

ከሊቁ ጋር የሚግባቡ ቢሆንም ናስር ጫት መቃም እንጂ ጠጅ ቤት ስለማይሄድ ሁለቱ ግን ቅዳሜ ከሰአት በኋላ ሲገናኙ ሌላ ሰው ግን እመካከላቸው ሳያስገቡ አብረው ተቀምጠው ጫት እየቃሙ   ማውራትን ይወዳሉ። ናስር ወደ ጉመሮ እንዴት እንደመጣ ሲናገር ቀበሌዎች በሆነ ባልሆነው እንደ በግ ታሰር ብለው ሲጎትቱኝ አጋሮ ትስፋቸው ብዬ ነው እዚህ የመጣሁት። ለካድሬዎቹ እኛ ያጣበብንባቸው ከተማ እኛ ስንለቅላቸው ይሰፋላቸዋል ብሎ ስለቀበሌ ተመራጮች ማውራት ከጀመረ አያቆምም። አስራ ሁለተኛ ክፍልን የጨረሰ ስለሆነ እንግሊዘኛም ጣል ጣል ማድረግ ያበዛል። ሊቁ አንዳንድ ግዜ በጣም ጠጥቶ ወደ ቤት አልገባም ካለ ናስር ብቻ ነው የሚያስገባው ተብሎ ይወራል።

ናስር ሰሞኑን በዚህ ጭንቅ ጉመሮን በወረረው ግዜ እድሉ ሆኖ አዲስ ትዳር ሊመሰርት የሚራወጥበት ወቅት ነበር። እጮኛው ጠጄ  ሻይ ለቃሚ ስትሆን ቆንጆና ታታሪ ከመሆኑዋ የተነሳ የሻይ ቅርጫቷን ስትሞላ ሌሎቹ ግማሽ አይደርሱም። ከናይለን የተሰራ አበባ ጣል ጣል ያለበት ቀሚሷ ጡቶቿዋን ወጥሮ ይዞ ልዩ ውበት ስለሚሰጣት እሷን ለማግኘት የማይመኝ ጎረምሳ የለም።ስትናገር ረጋ ያለችና አይናፋርም በመሆኑዋ ጎረምሳዎች እሷን ለመጠጋት ችግር ነበረባቸው።ናስር የትራክተር ሾፌር ስለሆነ ያንን እድል በመጠቀም ነው ሊተዋወቃትና ሊቀርባት የቻለው።በተለይ በሰራተኞቹ ካንፕ ውስጥ አንድ መጠጥ የጠጣ ሰራተኛ ከዚህ በፊት ትንሽ ቢተናኮላት በገጀራ ካሯሯጠችው በኋላ ማንም ቢሆን ማን ካለሷ ፈቃድ ምንም ነገር ለመሞከር የሚደፍርም አልነበረም።ጠጄም እንደ ናስር አጋሮ አካባቢ ቶባ ተብሎ ከሚጠራ ትንሽ ከተማ ነው የመጣችው። ወደ ጉመሮ የመጣችበት ምክንያት ታናሽ እህቷ ባል ልታገባ ስለሆነና እሷ ባል ስላላገባች የሰፈሩ ሰው ወሬ አላስቀምጥ ብሏት ነው ይባላል። አሁን ግን ከሰርጉ በኋላ ሁለቱም ተያይዘው ወደ አጋሮ ሄደው ዘመድ አዝማድ ለመጠየቅ ተስማምተዋል። ጠጄ  እንደሌሎቹ ሻይ ለቃሚዎች የዝናብ መከላከያ ላስቲኳን የትራክተር ሾፌር እጮኛ ሰለሆነችና ስለማትይዝ ወደ ስራ በምትሄድበት ግዜ ሁሉም ጎረምሶች እንደሚያዩዋትም ሰለምታውቅ አካሄዱዋን ታሳምረዋለች።እሷ ባለፈችበት ቦታ ለከፋና ፉጨት የማይቀር ነበር።እንደ ሁሉም የትራክተር ሾፌር እጮኛ ወይም ሚስት ምንም ግዜ ቢሆን ኃይለኛ ዝናብ ቢጥል ትራክተሩ ጋር የመጠለል ቅድሚያ ሰለአላት ያንን ትልቅ የሆነ የዝናብ መጠለያ ላስኪትና የሻይ መልቀሚያ ቅርጫት ጀርባዋ ላይ ተሸክማ አትዞርም።አሁን ግን ከናስር ጋር ያላት ግኑኝነት ከታወቀ በኋላ ፉጨቱም ፣ለከፋውም በጣም ቀንሷል።

ናስር ጠጄ ደስታን በዚህ ምድር አይኖርም ብዬ በሰማይ ስፈልግ በምድር ከሷ አገኘሁ ብሎ በኩራት ሰለሷ ማውራት ይወዳል።በቀበሌ እስር የላሸቀውን አዕምሮዬን እንደገና ብሩህ ተስፋ እንድመለከትና ለወደፊት እቅድ እንዲኖረኝ የምታደርገኝ አስተማሪዬም ነች ማለትን ያዘወትራል።

የናስር ጓደኛ አይሁን እንጂ ገረመው የሊቁ የማታ የማታ ጓደኛው ነው። ገረመው ጉመሮ ሻይ ልማት መዝገብ ቤት ውስጥ ተቀጥሮ የሚሰራ ሲሆን ጠጅ መጠጣት ስለሚወድ እሮብ ገበያ ያሉ ጠጅ ቤቶች ከመሸ የሚያጣው የለም። አጭር ፣ሁል ግዜ ካኪ ሳርያን የሚለብስ፣ ቆንጆ የሆነ እጅ ጽሁፍ ያለው ሲሆን ጉመሮ ከመቀጠሩ በፊት የጎሬ የታወቀ ራፖር ፀሃፊና እሱ የጠመጠመውን የታወቀ ጠበቃም እንኳ አይፈታውም ተብሎ የተነገረለት ነበር። ማታ ማታ እሱ ያለበት ጠጅ ቤት የቢሮ ውስጥ አዋቂ ነው ተብሎ ስለሚገመትና አንዳንድ ሰራተኞች ከቢሮው አካባቢ ጉዳይ ካላቸው እሱን ለማማከር ወይም እሱ ሲያወራ ለመስማት የሚመጣው ይበዛል። በጊዜ እንዳይገባና ጠጅ ቤቱ ባዶ እንዳይቀር የጠጅ ቤቱ ባለቤት ገረመው ጋባዥ ካጣ እራሱ ይጋብዘዋል። የገረመው የቅርብ ረዳት የሻይ ተክሉ ተላላኪ ታሪኩ ይባላል።

ታሪኩ ጥቁር ቀጭን ሲሆን ሁልግዜ መሮጥን ስለሚያበዛ ነው ተላላኪ ሆኖ የተመደበው። ድሮ ሻይ ጠባቂ በነበረበት ዘመን በዝናብ ግዜ ዛፍ ስር ሲጠለል አብሮት የነበረውን ጓደኛውን መብረቅ መቶ ስለገደለው በዝናብ ግዜ ስለመብረቅ ሲያስብ በፍርሃት ይንቀጠቀጣል።

ሰሞኑን ጉመሮ በሁለት ነገር እየታመሰ ነው።የናስር ሰርግ ስለቀረበ ሁሉም የሚችለውን እንዲሰጥ አየተጋበዘ ሲሆን የጉመሮ ሰራተኞች በሰርጉ ቀን ስለ አለው ዘፈን ደስታና መጠጥ በማስብ ውይይት ቢያደርጉም በሌላ በኩል ደግሞ ግቢው ውስጥ የተናፈሰው ከዋናው መስሪያ ቤት የሚመጡት እንግዳ ጉዳይ በሁሉም ላይ ጭንቀት ፈጥሯል።

በጣም የሚወራው ግን አቶ አስፋው የሚባል የዋናው መስራያ ቤት አላፊ ከአዲስ አበባ ይመጣል የሚለው ያልተጣራ ወሬ ነበር። ስለደረቀው ሻይ ሊመለከት አቶ አስፋው ይመጣል የሚለው መልክት በእርሻው ተክል መገናኛ ራዲዬ እንደተሰማ ገረመው ይህንን ጉዳይ ለተላላኪው ለታሪኩ ይነግረዋል። ታሪኩ ወሬውን ምንም በደንብ ሳያዳምጥ ለናስር ለትራክተር ሾፌሩ የጠፋውን ሻይ ተመልክተው ውሳኔ ለመስጠት ከዋናው መስሪያ ቤት ኮሚቴ ይመጣል ብሎ ያቀብለዋል። የስርጉን ጉዳይ ለማስተካከል የሚራወጠው ናስር እግረ መንገዱን ይህንን ወሬ በጠቅላላው ግቢ ውስጥ ያዳርሰዋል። በእዚህ አይነት ሁኔታ ወሬው ከላይ ወደ ታች ከታች ወደ ላይ እያለ ተስፋፋ።

የጉመሮ ሰራተኛ ምን እንሆን ይሆን ነገ በማለት መጨነቅና በየቦታው ወሬው እያደገ እያደገ ሄዶ ሌላ አዳዲስ ዜናዎች ጨምሮ መወራት ይጀመራል። ሰራኛው ሁሉ ወደ ጋምቤላ ሊላክ ነው እዛ የበቆሎ እርሻ ይጀመር ብለዋል እሳቸው የሚልም አለ። ሌላው ወደ ደዴሳ ልንላክ ነው ይላል። አንዳንዱ በበቃ ቡና ለመልቀም ስው ስለሚያሰፈልግ ልንሄድ ልንላክ ነው ይላል። ግቢው አንድ ግዜ በተለያየ ወሬ ተሞላች።

የግቢው አላፊዎች አቶ አስፋው ስለሚመጣ ለመዘጋጀት ማለትም መጠጥ ስጋ እና አንዳንድ የሚስፈልግ ጉዳይ ለመግዛት ብለው በዛውም ደግሞ ጎሬ ቢራ መጥቶል ተብሎ ስለተወራ ማለትም በዛ ግዜ ቢራ በወረፋ ለአውራጃ ከተማዎች ሰለሚላክና ከአንድ ቀን በላይ ሰለማይኖር ቢራ መጣ ከተባለ ሄዶ መጠጣት የተለመደ ነበርና ይህንን ጉዳይ አስታከው ወጥተዋል።

ቀኑ መምሸቱ አይቀርምና የእሮብ ገበያ ካለወትሮዋ እየሞላች መጣች። ጠጅ ቤቱም ሞቀ። እነገረመው የክብር ቦታቸውን ይዘው ተሰየሙና የሁሉም ጨዋታ ከዋናው መስሪያ ቤት የሚመጡት እንግዳ ይሆናል ተብሎ በገረመው አካባቢ ትኩረት ተደረገ። እያንዳንዱ አውጥቶ ለምን እንደመጣ አይናገር እንጂ ሁሉም የገረመውን ማሳረጊያ ንግግር ለእውነቱ የሚቀርበው ነው ተብሎ የሚጠበቀውን ለመስማት ነበር ዛሬ እሮብ ገበያ የተጥለቀለቀችው። ገረመውም ቢሆን ይህንን ጉዳይ ስለሚያውቀው ወሬውን ሳይጀምር የሚመጡት ሰዎች እየተቀበለ ምንአልባት ለጫዋታው ማማር የግብዣው ብዛት ወሳኝ መሆኑን በሚገልፅ ፈገግታ አልፎ አልፎ ለእያአንዳንዱ ያሳያል። ወሬውን

ለመቀየር የሚደረገውን ጥረት እያከሸፈ ወደ ሌላ ወሬ እየቀየረ ግዜውን ያራዝመው ነበር። ገረመው በዚህ ግዜ ነው ለገሬ አንድ ስጭው በተባለ  ቁጥር በፈገግታ ጋባዡን ካመሰገነ በኃላ አጠገቡ ከተቀመጠው ከሊቁ ጋር ስለዝናብ መጥፋት በተለያዩ አመታት ስለነበረው ዝናብ ወሬውን ይቀጥላል።

ሊቁ ከዋናው መስራቤት የሚመጡት እንግዳ እንደ ሻይ ልማቱ ሰራተኞች ባይጠብቅም ዛሬ ጠጅ ቤቱ የሞላበት ምክንያት ግን አንድ ታላቅ ወሬ እንዳለ ስለተረዳውና ገረመውን የሚጋብዙትም ለሊቁም እስቲ አንድ በሉልኝ እያሉ በተላላፊ ይጋብዙታል።

ሊቁ ታዲያ በዚህ ምሽት ሬዲዮኑን መክፈት አልፈለገም ይህ ሁሉ ሰው ተሰብስቦ ጨዋታው ሞቆ ግብዣው በሚፈስበት ግዜ የሱን ራዲዮ ቢያወጣ ማንም የሚሰማው ሰለሌለ ለዛሬ ጠጁ ላይ ትኩረት ሰጥቶ ጨዋታውን ከገረመው ጋር አመሳስሎ ምሽቱን እየተደሰተበት ነበር። ሊቁ ትንሽ ሲጠጣ እኔ ያራዳው ልጅ ብሎ እዚህ ወድቄ ቀረሁ ብሎ ምርር ብሎ እንደሚያለቅስ የታወቀ ስለሆነ ጋባገሮቹ ሁሉ ብዙ እንዲጠጣና እንዲሰክር አይፈልጉም ነበር።

ሊቁ በዚህ ምሽት ከገረመው ጎን ተቀምጦ የሚደረግለት ግብዣ በገረመው ምክንያት መሆኑን ስለተረዳ ቢይጥመውም ባጥመውም የጫወታው ተካፋይ ሆኑዋል። አንዳንዴ አርዕስቱን ቀይሮ ብዙው ጠጪ ወደሚጠብቀው ሊቁ ለመቀየር ያደረገውን ሙከራ ገረመው ካለ ምንም ችግር አስቁሚታል።

መጠጡ እየተጠጣ ጫዋታው ሞቆ አንዳንዴ ሲደበላለቅ አንድ በእድሜያቸው ገፋ የሚሉ አባ እሸቱ የሚባሉ ሽማግሌ ካለወትሮአቸው ብዙም ሳይጠጡ ቆይተው ጮክ ብለው ልጅ ገረመው ምነው እባክህ ምን እንደሚያስጨንቀን እያወቅህ ዝም ትላለህ የምታውቀውን አትነግረንም ሲሉ ጠቅላላ የሚንጫጫው ጠጭ በሙሉ ዝም ብሎ የገረመውን መልስ ይጠብቅ ጀመር። ገረመው ሰው እሱ እንደሚጠብቀው እንዳላወቀ አይኑን ጎልጎል አድርጎ፤ ለምን አልነገራችሁኝም እኔ ምነው አለወትሮው በስራ ቀን ቤቱ ምነው ሞላ ብዬ ሳስብ ነበር ብሎ ገረመው ሁኔታውን እንዳልተራዳ ለማድረግ ያደረገውን ሙከራም ማንም አላመነውም። መቼስ አዲስ ነገር ስለሌለ ነው እንጂ ቢኖርማ ቀድሜ አደለም የምነግራቸሁ ብሎ ጠጁን አንስቶ ሲያንቆረቁር ሽማግሌው እንደገና ጮክ ብለው ምንድነው የምንሰማው ከዋናው መስሪያ ቤት የሚመጣ እንግዳ ሻይ ተክሉን ሊዘጋው ነው አልተባለም እንዴ? ብለው ጠየቁት ። ገረመው ሁኔታው ምንም የሚያስመልጠው እንዳልሆነ ሰላወቀና ትንሽም መናገርና ማጓጓት ሰላለበት እሱማ እውነት ነው ማን ማን ይምጣ ለምን ይምጡ የምናውቀው ነገ ነው። ነገ አራት ሰአት ላይ እሬዲዎኑ ሲከፈት ነው ብሎ አቆመ።

ከልምድ ሁሉም ከዚህ በላይ ገረመውን መጠየቅ መልስ እንደማያገኙ ስለሚያውቁት እሱን ትተው ሁሉም የግላቸውን ጫዋታቸውን ቀጠሉ። ግማሹ እነከሌ ይመጡ ይሆናል ሲሉ ሌሎቹ ደግሞ አይሆንም ይላሉ። ግማሹ ደግሞ ጎጀብም ከመዘጋቱ በፊት እንደዚህ ነበር ሲል ሌላው እያንሾካሸከ እሳቸው ሲዳሞ ሄደው የዘጉት በእንደዚህ ነው ይላል ። ግን ለማንኛውም ሁሉም ነገ ገረመው እዚህ እንደሚመጣ እየጠየቁት መውጣት ጀመሩ።ግን ላፋቸው ያህል ጠየቁት እንጂ ለነገሩማ ገረመው እዛ እንደማይጠፋ አጥተውት አደለም ።

ሊቁና ገረመው በተትረፈረፈው ግብዣ ጠጥተው በዚያ በጨለማ እንደተለመደው እየተከራከሩ ወደየቤታቸው አመሩ።

- አታውቀኝም እንጂ የሊጉ አባል ነበርኩ። እዚህ መውደቄን አትመልከት። አለ ሊቁ
- ሊቅ መሆንህን ሁሉም ያውቃል አለ ገረመው።
- ሊቁ እየተንገዳገደ መዘመር ጀመረ።

ቀኑ ደርሷል ሊነፋ መለከት
ህዝብ ይጠራል ካለበት በድንገት

**ተስብሰበን ልንቆም ........ ብሎ እንደተለመደው ይኮላተፍ ጀመር።የመጨረሻውን ቃል ማንም ሰምቶት አያውቅም።**

- **አንተ የምትለው ቀን ምንግዜም አይደርስም። የተሰፋ እንጀራ ነው። አለ ገረመው**
- **ዝም በል ምን ታውቃለህ ጎማ ሙሉ ፈስ እያለ እየተሳደበ ወደ ቤቱ ገባ።**

**በልጅግ አሊ**
**ይቀጥላል**